የወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና ወሲባዊ ትንኮሳ (SEAH) መነሻ ምክንያቶች

በ ወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና ወሲባዊ ትንኮሳ "መነሻ ምክንያቶች" እና "የተጋላጭነት እና የአደጋ ምክንያቶች" መካከል ልዩነት አለ።

የተጋላጭነት እና የአደጋ ምክንያቶች በአንድ ግለሰብ አካባቢ ውስጥ የሚገኙ ለወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና ወሲባዊ ትንኮሳ የመጋለጥ እድላቸውን የሚጨምሩ ሁኔታዎችን ያመለክታሉ። ለምሳሌ ደህንነቱ የተጠበቀ የግል ማረፊያ እጦት ሴቶችን ለወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና ወሲባዊ ትንኮሳ ከፍተኛ ተጋላጭነት ሊያጋልጥ ይችላል ምክንያቱም ለጥፋት ፈጻሚዎች ወደ እነዚህ ቦታዎች ለመግባት ቀላል ስለሆነ።

መነሻ ምክንያቶች በተቃራኒው፣ ጥፋት ፈጻሚዎች ወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና ወሲባዊ ትንኮሳን ያለ ምንም ቅጣት እንዲፈጽሙ የሚያስችላቸውን የስልጣን ኃይል ሚዛን መዛባት የሚፈጥሩ ነገሮችን ያመለክታሉ። ለምሳሌ፣ አንድ ግለሰብ መሠረታዊ ፍላጎቱን ለማሟላት በእርዳታ እደላ ላይ ጥገኛ ከሆነ ለወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና ወሲባዊ ትንኮሳ አደጋ የበለጠ ሊጋለጥ ይችላል።
ለዚህ የስልጣን ኃይል ሚዛን መዛባት አስተዋጽኦ የሚያደርጉ ምክንያቶች በሁለት ዋና ዘርፎች ይከፈላሉ:

1. ግለሰቦችን ወይም ቡድኖችን ከህብረተሰብ እና ከስልጣን ለማግለል ወይም ለመጉዳት የሚያገለግሉ **ሥር የሰደዱ፣ ተመጣጣኝ ያልሆኑ እና ጎጂ ባሕላዊ እና ማህበራዊ ደንቦች**። እነዚህ ደንቦች ብዙውን ጊዜ የአንድን ሰው ማንነት ወይም እንደ ጾታ፣ ሥርዓተ ጾታ እና የሥርአተጾታ መለያ፣ ጾታዊነት፣ የአካል ጉዳተኝነት፣ ዘር ወይም ሀይማኖት ያሉ ባህሪያትን መሰረት በማድረግ መድልዎ ሊያስከትሉ ይችላሉ።

2. ፍትሃዊ ያልሆነ የሃብት ክፍፍል። በስልጣን ኃይል ላይ ያሉት የሀብት ክፍፍልን ይቆጣጠራሉ። ግለሰቦች በልዋጭ "ውሲባዊ ጥቅሞች"ን ለማግኘት ሴቶችን እና ልጃገረዶችን ጠቃሚ ሀብቶችን ከማግኘት በመከልከል ስልጣናቸውን አላግባብ ሊጠቀሙ ይችላሉ። እነዚህ ሀብቶች ምግብን፣ መጠለያን፣ ገንዘብን እና ውሳኔ መስጠትን ሲያካትቱ፣ ነገርግን በእነዚህ ብቻ አይገደቡም።

ኃይል እና ልዩ መብት

- ሥርዓተ ጾታ እና ማህበራዊ ልማዶች
- ወደ ማግለል እና ተጋላጭነት የሚመሩ ማህበራዊ ተዋረዶች
- በመደብ ፣ በዘር ፣ በጎሳ ዙሪያ ያሉ እምነቶች።



የአደጋ ምክንያቶች እና የወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና ወሲባዊ ትንኮሳ መነሻ ምክንያቶች: በግለሰብ፣ በማህበረሰብ፣ በድርጅት እና በመዋቅር ደረጃ



አንድ ግለሰብ በሰፊው አካባቢ እና ማህበረሰብ ውስጥ ይኖራል። የወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና ወሲባዊ ትንኮሳ ስጋትን የሚጨምሩ ምክንያቶች በእያንዳንዱ ደረጃ (መዋቅራዊ፣ ማህበረሰብ፣ ድርጅት፣ ግለሰብ) ይገኛሉ፣ እንዲሁም ብዙ ጊዜ በማህበራዊ ደንቦች የተደገፉ ናቸው።

በግለሰብ ማንነት እና በአካባቢያቸው ባሉ ማህበራዊ ደንቦች መካከል ያለው መስተጋብር የኃይል ስርጭትን እና ተደራሽነትን ለመወሰን ወሳኝ ሊሆን ይችላል።

የኃይል እና የልዩ መብት ጉዳዮች የሁሉም የወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና ወሲባዊ ትንኮሳ ዓይነቶች መነሻ ናቸው። በጣም ለጥቃት የተጋለጡ እና የወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና ወሲባዊ ትንኮሳ ስጋት የተጋረጠባቸው ተብለው የተለዩ ቡድኖች በብዛት በየአውዳቸው ውስጥ አነስተኛ የስልጣን ኃይል እና ልዩ መብት የያዙ ናቸው። ሰዎችን በጾታቸው፣ በሥርዓተ ጾታ፣ በጾታ ማንነታቸው፣ በዘራቸው፣ በመደባቸው፣ በወሲባዊ ዝንባሌያቸው እንዲሁም በጎሳቸው ላይ በመመሥረት የሚያገልሉ ማህበራዊ እና ድርጅታዊ ደንቦች፣ እንደነኚህ ዓይነቶቹ ባህሪያት እጅግ የተለመዱ የሆኑበት ጥፋተኛ ሰዎች ከቅጣት የሚያመልጡበት ባህል አካላት ናቸው።

በዕርዳታው ዘርፍ ውስጥ፣ ግለሰብ የማህበረሰብ አባላትን እና የእርዳታ ሰራተኞችን ለአደጋ የሚያጋልጥ የስልጣን ኃይል አለመመጣጠን አለ። በእርዳታው ዘርፍ ውስጥ ወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና ወሲባዊ ትንኮሳን ለማስቀረት እነዚህን መነሻ ምክንያቶች ተገንዝበን መቃወም እና አዳዲስ ደንቦችን ለመመስረት በጋራ መስራት አለብን።

በዚህ ጉዳይ ላይ ለበለጠ መረጃ እባክዎን **የመነሻ ምክንያቶች ማስረጃ ጥንቅር** እና **ሥልጣንን ያለአግባብ መጠቀም** **በሚሉ ርእሶች ያዘጋጀናቸውን ግብዓቶች** ይመልከቱ።